## ይድረስ ለአቦ አራዳ ሻውልና ለዶክተር አበባ ፈቃደ

## ምን ቦጣን በጎጥ ተተብትቦ ወደኋላ !

ከ -- ሀገሬ አድማሱ

ሁለታችሁም የምትደነቁ የሀገር ዜጋዎች የምትፅፉት እንግሊዝኛ ከአቅም በላይ ሆኖ ቢያንገዳግደኝም የአቅሜን ለመረዳት ሞክሬ የበኩሌን አንዳንድ ልል ተነስቻለሁ::

ኦቦ አራዳ አቅጬን ቁጭ አድርገኸዋል:: ሻዕቢያ በጆግራፊ ሲገዛ፤ወያኔ ደግሞ በባዮሎጂ ወይም በውልደት ወይም በጎጥ/ዘር ይገዛል:: ኢሕአፓ ደግሞ በርዕዮት ተገዢ ነው ተብሎ ተቀምጧል:: ይህ ንጥረ ሀሳብ በሀቅ ላይ የተመሰረተ ነው:: በአሁኑ ጊዜ በወያኔና በሌሎች መሀል ያለውን ልዩነት ያጠቃልላል፤ይገልጥልናል:: እነ ኦነግም ቢሆኑ በዚሁ በወያኔ መልክ የሚፈረጁ ናቸው:: ዶክተር አሰፋ ነጋሽ የተባለው ግለሰብ ለምሳሌ ፖለቲካ ገለፃው/መፅሀፉ ባዮሎጂ ላይ የተመሰረተ ነው--ልክ እንደ ወያኔ:: ኢትዮጵያን ማዳኑ ሆነ ግንባታው ይህን ሀቅ ወይም ምርጫ የሚዘነጋ ሊሆን አይችልም ይመስለኛል መልዕክቱ:: ሀገር ማዳን ራሱ መጀመሪያ ሀገርን በምን ደረጃ እንደምንገልጥ ማወቅን ጠያቂ ነው ማለት ነው:: በጂዮግራፊ ወይም ክልል/ድንበር መሰረት? በውልደትና ጎጥ? ወይስ ሁሉን አቀፍ በሆነ ዘመናዊና ዴሞክራሲያዊ ራዕይ መሰረት?ሀገር ስንልስ ሕዝቧን ነው ወይስ መሬት ድንበሯን ብቻ? ሕዝብስ ስንል ባለው እንዳለው ወይስ ጭቁን የተባለውን ሕዝብ? በነዚህ  ጥያቄዎች ላይ እንድናስብ ኦቦ የገፋፉን መሰለኝ::በደፈናው ሀገር ማዳን የለምና በአቶ ሀማም ፅሁፍ እንደተገለጠው:: በእርግጥ አመለካከትና ፍረጃ በመሰረቱ ከመነሻው ሊለያይ ይችላል:: ለአቶ ሀማና ኦቦ ለምሳሌ መደብ ቀዳሚ የሆነ ይመስላል:: ለዶክተር አበባ ደግሞ ማጣቀሻቸው ኢትዮጵያዊነት የተባለ ፅንስ ሀሳብ ሆኖ ይገኛል::

ዶክተር አበባ ዶክተርነትዎን ከዋሽራ ሳይሆን ከባዕዳን ያገኙ በመሆንዎ ለምን ዘመናዊ ትምህርት ላይ በአሉታዊ ተነሱበት ማለት አይቻልም:: መብትዎ ነው:: ግን ትችትዎ እስከገባኝ ድረስ የተማረውን ትውልድ፤ ለሀገሩ ለለውጥ የታገለውን ትውልድ (ድርጅት?) የሚወቅስ ይመስላል:: ለእርስዎ ኢትዮጵያን ለመለወጥ የታገለው ትውልድ ኢትዮጵያዊነትን በሚገባ አላንፀባረቀም:: ይህን የሚሉት አንድም የምዕራቡን ትምህርት ወይም ርዕዮተዓለም በመከተላቸው ነው ሲሉ ( የምዕራቡ ትምህርት የሀበሻውን አንጎል ቅኝ ገዛው ባይ ኖትና) በሌላ በኩል ደግሞ ለእርስዎ ኢትዮጵያዊነት ራሱን የቻለ ፤ የባዕድ ትምህርትና ግንኙነትን ያራቀ የኢትዮጵያ ታሪክና ቅርስ ላይ የተመሰረተ ነው:: ይህን ታሪክና ቅርስ በማድነቅም ኢትዮጵያን ልዩ ሀገር ያደርጓታል::  እኛ ሀበሾች! ቃና አለው አቀረራብዎ:: ይህ ደግሞ ወደ መጥፎ ስሜት (ዘረኝነት) እንደሚያመራ አፍሪካውያን ወንድሞቻችንን መጠየቅ የለብንም:: ቁርጥ ኢትዮጵያዊ! ቁርጥ ሀበሻ የሚለው ያው ጠቆር ያልነውን የሚጠቀልል አልነበረም፤ አሁንም ለብዙዎች አይደለም:: ስለዚህም ይህ የኢትዮጵያ ቅርስ መለስ ዜናዊ እንዳለው ለእኛ ምን ገዶን የምንለው አይደለም ብንልም በደፈናው ግን በፀጋነት  ወይም ነገን በመገንቢያ መሰረት አድርገን የምንወስደውም አይደለም :: ታሪክ ከተባለም ዘመናዊ ትምህርትን በማስገባት ወይም ለምዕራቡ ስልጣኔ በጎ

ዕይታን በመያዝ የመጀመሪያው አፄ ኃይለ ሥላሤ አልነበሩም፡፡ ያለፉት ስርዓቶች በሞላ ኋላ ቀርና ጨቋኝ ነበሩ፡፡ ጃፓን የሰለጠነችውም ሚቼ አቶ ከበደ ሚካዔል ባቀረቡት ዓይነት ብቻ ሳለመሆኑ ዛሬ ምስክር ነው፡፡ ለምሳሌ  የጃፓን ህብረተሰብ ከአፀያፊ ዘረኝነቱ ጋር እስካዛሬ መቆየቱም የሚያኮራ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከምዕራቡ ጠቃሚውን መውሰድ የማይበጀውን መተው ነውና ዋናው ጥያቄ፡፡

ለዚህም ነው የራዕይ ጉዳይ፣ሀገርን ከሰፊው ሕዝብ አንፃር ማየቱ ና የወደፊቱን ገፅታዋን በዚሁ መሰረት ለመቃኘት መነሳቱ አስፈላጊ የሚሆኑት፡፡ ኦቦ ወደፊት ሲያይ ዶክተር አበባ ወደኋላ ያያሉ፡፡ ኦቦ ምሁሮችን ሚና ሲሰጥና ሲያደንቅ ዶክተ ር አበባ የተማረና የታገለውን ቅኝ ተገዛ ብለው ያወግዛሉ፡፡ ኦቦ አራዳ ዕይታው/ራዕ ዩ ሰፊ ነው፡፡ ዶክተር አበባ ኢትዮጵያ ቢሉም ራዕያቸው ጠባብ ነው--ያለፈውን መላሽ ለመሆን ሲነሱና የእነዚያን ጊዜዎች አስከፊ ስርዓቶች ለመመለስ ሲመኙ ከብ ዙሃኑ ይነጠላሉ፡፡ ፈለጉም አልፈለጉም ወደ አንድ ጎጥና ሀይማኖት መመለሳቸው የማይቀር ይሆናል፡፡ ስለዚህም የኢትዮጵያዊነት ገለፃቸው ወይም ትርጉማቸው ይጠባል፣ ድንጋይ ዳቦ ዘመንን ይመኛል፡፡ ለለውጥ የታገለው ትውልድ ግን ኢትዮጵ ያን አፍቅሮ በዓይኗ ያለውን ግንድ፣ ቆንጆ ገፅታዋን ያጎደፈውን ሁሉ ሊቀይር የተነ ሳ ነበርና የኢትዮጵያዊነት ዋና ነፀብራቅ ነው፡፡ በፊት እንዳልኩት  ይህን ጠበቅ ባለ መንገድ (አቶ ሀማ) ወይም በሌላ ማየት ሊኖር ይችላል ግን ያን ትውልድና ዛሬም ኢትዮጵያን ሊለውጥ ሊያሻሽልና ዘመናዊ ሊያደርግ የተነሳውን ትውልድ መንቀፉ ስህተት ነው፡፡

ዶክተር አበባ ሆኑ ኦቦ አራዳ (እኔም ከእነሱ ባነሰ ደረጃ) የምዕራቡ ትምህርት ውጤ ት ነን፡፡ ይባል ካልንማ ዶክተር አበባ ፅሁፋቸውን በእንግሊዝኛ እንጂ በአማርኛ አላቀረቡልንም፡፡ ለዚህ እሳቸው እንጂ እኔ ብዙ ቦታ አልሰጠውም፡፡ ኦቦ አራዳ ሀቁ ን ተቀብሎ ከኢትዮጵያዊነቱ ጋር አጣጥሞ ሲገኝ ዶክተር አበባ ግን ይህ ያቃትዎ ይመስላል፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን የራሳችን ኩራት (ያውም በዛ የሚባል) ያለን ሆኖ ሳለ የዝቅተኛነት ስሜት ወደ ፈጠረውና በተለይም በአፍሪካን አሜሪካኖች ወደ ሚንፀባረቀው የስልጣኔ አራማጅና ማዕከል ጥቁሮችና አፍሪካ ናቸው (ለእርሰዎ ደግሞ ኢትዮጵያ ናት) ወደሚለው ዕንፍ በመሄድ መጥፎም ጥሩም ያለውን ቅርስ ዕፁብ ድንቅ ወደማለቱ ወርደዋል፡፡ ይህ ደግሞ ትምህርትዎ ወይም ስምሪትዎ ያመጣው  ሊሆን ቢችልም ኢትዮጵያን ለመውደድ የስልጣኔ ጀማሪ ናት ብለን መነ ሳቱ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ ድንቅነሽ ባትገኝም ኖሮ ኢትዮጵያን ልንወዳት እንችላለ ን ማለት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ የረሀብና ችጋር ምሳሌ ሆነ በመገኘቷ ሞራላ ችን ወድቆ እየረዱን ላሉት ባዕዳን ገና የእናንት ሀገር ሳይሰለጥን ኢትዮጵያ ሰልጥና ነበር ብሎ መጮኹ አስፈላጊ አይደለም፡፡ የማይደበቅው ሀቅ ዛሬ ሀገራችን ያለችበ ት ሁኔታ ነው፡፡ ሕዝብ ከዚህ ችግር መላቀቅ ይፈልጋል እንጂ ያሳፍራል ፣ጉዳችን አይወራ፣ ደብቁ አይልም፡፡ይህን ለውጥ ደግሞ የጥንቱን ዘመን ፈልጎ  ወይም ዛሬን ጠልቶ፣ ዘመናዊ ትምህርትን አውግዞ የምናገኘው ሊሆን አይችልም፡፡ ቻይናም፣ ህንድም፣ ጃፓንም የደረሱበት ቦታ የደረሱበትን መንገድ ስናይ በደፈናው የምዕራቡ ን ትምህርት በማንኳሰስና ባለመቀበል አይደለም፡፡ ቻይና ደግሞ ከአሰቃቂ ስርዓት የተላቀቀችው ምናልባትም ዶክተር አበባ ባዕድ ብለው በሚያወግዙት ርዕዮት ተመርታ መሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡

የድሮውን ስርዓት ሆነ አስተሳሰብ በመመለስ ኢትዮጵያን ማዳን አንችልም፡፡ አዲሲቷ ኢትዮጵያ በሕዝብ እኩልነትና በዴሞክራሲ ላይ መመስረት አለባት፡፡ በአዌነትና በኋላቀርነት ላይ ሳይሆን፡፡ ኢትዮጵያዊ ብሄራዊ ስሜትመ መገንባት ያለበት በዚሁ መንፈስ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከዓለም ተነጥላ “ ዓለምን ረስታ በዓለምም ተረስታ” ትኖር ዘንድ መመኘትም ቅዠት ነው፡፡ የዓለም አካል ናት፡፡ በዚች ዓለምም ኢትዮጵያ የበኩሏን ታበረክት ዘንድ ተገቢ ቦታዋን እንድትይዝ ነው መታገል የሚገባን፡፡ ዶክተር አበባ የሚመኟት ኢትዮጵያ ልትመጣ ካለመቻሏ ሌላ እንድትመጣም በበኩሌ አልፈልግም፡፡ ወደ ኋላ መሄድ ከመቸ ወዲያ ዕድገት ተባለ? ለውጥ የህብረተ ሰብን ህግ ተከትሎ የሚመጣ ነው፡፡ የለውጥን ማዕበል በጠቃሚ ፈለግ ለማፍሰስ መጣር ግን ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ ባልነቁ ባልተማሩ የሚከናወን ሳይሆን ነቅተው በሚታገሉና በተለይም በተደራጁና ሕዝብን ባቀፉ ክፍሎች ነው፡፡ ሌላ መንገድ የለም፡፡ ለዚህም ነው የተፈጥሮን ወይም የህብረተሰብን ዕድገት ህግ ማለትም ለውጥን ተፃረው የሚገኙ ወግ አጥባቂዎች ሁሉ ልፋታቸው ከንቱ ሆኖ የሚገኘው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከችግሩ ነፃ የሚወጣበትን፣ በበቂ የሚመግበትን፣ መብራትና ንፁህ ውሀ የሚያገኝበትን፣ ልጆቹ ትምርት ቤት ገብተው የሚማሩበትን፣ መብቱ የሚከበርበትን ማለትም በጥቅሉ በተለይ በተመቻቸ ሁኔታ ባዕድ ሀገር ያለነው የምናገኘውን ማግኘት ይፈልጋል፡፡ ኩራዝ መብራት እንኳን አጥቶ፣ በደሳሳ ጎጆ ጠሙን እያደረ በትኋን መበላት፣ በቀላል በሽታ ልጆቹን መቅበር ተገዶ መኖር አይሻም፡፡ የፈረንጁ ይቅርብህ የሚሉት የፈረንጁ አልቀረባቸውም፡፡ ስልጣኔ የዐላም ህዝብ ሁሉ የጋራ ውጤት ነው፡፡ የህገራችን በሙጀሌ ከሚመዘመዝ ጫማ ይፈልጋል፡፡ ለበሽታው መድህኒት ይፈልጋል፡፡ የምዕራቡ ይቅርብህ ባዮች መድህኒት አንውጥም፣ ጠበል ይበቃናል ሲሉ አልሰማንም፡፡ በርግጥ ቅርስ በአዎንታዊ ያኮራል ግን በብቻው ከችግር አያድንም፡፡ ሰው በእንጀራ/በዳቦ/ ብቻ አይኖርም የሚሉ ለምን ብዙውንጊዜ እንጀራ ያላጡት ናቸው ብለን መጠየቅ አለብን፡፡ ለሕዝባችን ደህንነትና ስብዓዊ ክብር የሚጠቅመውን ሁሉ መፈለግ አለብን፡፡ ለዚህ ደግሞ ንጉስ ኤዛናና አፄ ልብነ ድንግልን መቀስቀስ አያስፈልገንም፡፡ ለነገሩማ እነ አፄ ልብነ ድንግል በፖርቱጋል ወጨፎ ባይታገዙ ኖሮ……………

የእኛ ጭንቀት የዛሬይቷ ኢትዮጵያ ናት፣ መሆን አለባት፡፡ ኢትዮጵያ ሕዝብ መከራና ስቃይ በጣም አሰቃቂ ነው፡፡ ከተቻለ ብሶቱን ዋይ ዋይታውን ልናውቅለት ይገባናል፡፡ ወይኔ ህዝባችን ተጎዳ እያልን ግን ሰቆቃውን በዚያው ወዲያው ረስተን የኢትዮጵያ “ ዝና ተዋረደ ” በሚል የምንጮህ ከሆነ (ገበናን ደብቁም በዚያው አጃቢ ሆኖ) ነገር ዓለሙን ስተነዋል ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ክብር ህዝቧ ሲከበር ነው፡፡ ሀገርን ማዳንም የሕዝብን ክብር ስናረጋግጥ ነው፡፡ ማለትም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሲመሰረትና ለውጥ ሲመጣ፡፡ በጆግራፊና ባዮሎጂ መገዛት፣ አንጎላችንን በቆሽታችን መተካት ስናቆም፡፡ የህፃናት መብት ሲከበር፡፡ እህቶቻችን ሳይሸጡና ሳይዋረዱ፡፡ አርሶ አደሩ ባለመሬትና ባለመብት ሲሆን፡፡ እኩልነት ሀቅ ሲሆን፤፤ የህግ የበላይነት ሲከበር፡፡ ወዘተ ዶክተር አበባ በሚመኙት ”ድሮ” ይህ ሁሉ አልነበረም፡፡ የዶክተር አበባ “ መድህኒት” አይጠቅምም፣ አደናጋሪም ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህም ነው በተወላገደ መንገድ የተማረው ያ የታገለውና እየታገለው ያለው ትውልድና ምሁር ሳይሆን ለሕዝብ ያልበጀን ዘመን የሚናፍቁት ራሳቸውና መሰሎቻቸው የሚሆኑት፡፡ ትዕግስቱን ከሰጣቸውም በተማሩት ተጠቅመው ቢመራመሩና ቢማሩ ጠቃሚ ይሆናል ብዬ በትህትና ለመጠቆምና በዚሁ ለመደምደም

እፈልጋለሁ፡፡

አቦ አራዳም ከሆነላቸው ቀለል ባለ እንግሊዝኛ ቢፅፉልን ጥሩ ይሆንልናል፡፡